የሰ/መ/ቁ 245928

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም.
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

<u>ሁለተኛ ሰበር ችሎት</u>

ዳኞች፡-

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- አርአያ ገ/ሚካኤል ገ/አምላክ ጠበቃ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ጅሩ መሃመድ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 244965 በቀን 05/8/2015 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 400855 በቀን 29/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የንብረት ጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ሃረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም የኢትጵያ መድን ድርጅት ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ታህሳስ 09 ቀን 2013 ዓ.ም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት የሰሌዳ ቁጥሩ 68355 ኦ.ሮ የሆነ ሚኒባስ መኪናቸውን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-847559 ኢ.ት በሆነ የአመልካች ተሳቢ መኪና በ27/05/2013 ዓ.ም ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ደንገጎ ቀበሌ ላይ ተገጭቶ በደረሰው አደጋ ምክንያት ብር 600,000.00 (ስድት መቶ ሺ ብር) የሚገመት ጉዳት የደረሰ ሲሆን በአሁኑ የገበያ ዋጋ መኪናውን ለማሰራት ብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊየን አምስት መቶ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸምዓለማአ የገለግልም!

ሺ. ብር)፣ እንዲሁም ሚኒባሱ ስራ በማቆሙ ምክንያት የተቋረጠብኝ ገቢ ብር 1,055,000.00 (አንድ ሚሊየን ሀምሳ አምስት ሺ ብር) የጠበቃ አበል እና የዳኝነት ክፍያ ጨምሮ በድምሩ ብር 3,050,000.00 (ሶስት ሚሊየን ሀምሳ ሺ ብር)አመልካች እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠው መልስም ጉዳቱን ያደረሰው ተሽከርካሪ ሙሉ የኢንሹራንስ ዋስትና ሰጭው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ወደ ክሱ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር፣ መኪናው ሳይሰራ የዘገየው ተጠሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጉዳት የደረሰበትን ሚኒባስ ተሽከርካሪ ወስጄ ላስጠግን በማለት ያቀረበውን አማራጭ አዲስ ካልገዛችሁልኝ በሚል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው፣ መኪናው ሊጠገን የሚችል በመሆኑ በሌላ መኪና ሊተካት አይገባም፣ መኪናው እንዲጠገን ተብሎ እንዲወሰን በማለት ክርክር አቅርቧል፡፡ ጣልቃገብም ሃላፊነት እንደሌለበት፣ አለበትም የሚባል ከሆነ እስከ ብር 700,000.00 ሊሆን እንደሚገባ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቀደም ሲል ግራቀችን አከራክሮ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳት የደረሰበት መኪና ሊጠገን የሚችል ነው ወይስ አይደለም? ሊጠገን የሚችል ከሆነስ ለጥገናው የሚያስፈልገው ወጭ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ነጥቦች አጣርቶ እንዲወስን ነጥብ አስይዞ በመለሰው መሰረት ፍርድ ቤቱ በተጠሪ መኪና ላይ የደረሰው ጉዳት ሊጠገን የሚገባ ስለመሆኑና ለጥገናው የሚያስፈልገውን ወጭ ከሞኤንኮ እና ሰይፉ ጋራዥ ከተባለ ድርጅት ሪፖርት አስቀርቦ ለጥገና 1,500,00 እዲሁም በተሽከርካሪው ላይ አደጋ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ለ10 ወራት የታጣ ገቢ ከገቢዎች ጽ/ቤት ማስረጃ በማስቀረብ ብር 141,828 በአጠቃላይ ብር 1,641,828.00 ከዚህ ውስጥ ጣልቃገብ በሰጠው የመድን ሽፋን ልክ 700,000 እንዲከፍል ፣ በአመልካች ለደረሰው ወጭ ኪሳራ የጠበቃና የዳኝነት ወጭዎችን ጨምሮ ንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀችን ሰምቶ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በነጥብ ከተመለሰለት ጭብጥ ውጭ በተሽከርካሪው ጉዳት በመድረሱ ምክንያት የታጣ ገቢ በሚል የወሰነው ተገቢነት የለውም በማለት ለመኪናው ጥገና የተወሰነውን 1,500,00 በማጽናት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ችሎቱም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 9(4)መ መሰረት ሁለተኛ ይግባኝ በመሆኑና ሁለተኛ ይግባኝ

የማቅረብ መብት የሌላቸው በመሆኑ ጉዳዩ በችሎቱ ሊስተናገድ አይገባም በሚል በብይን መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአመልካች ይህ የሰበር አቤቱታ ሚያዝያ 18 ቀን 2015ዓ.ም ተጽፎ የቀረበውም የይግባኝ ችሎቱ የሰጠውን ብይን እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ የተለየ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ9(4) መሰረት በተለወጠው ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው በመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከዚህ አንጻር ያቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ድጋሚ ይግባኝ ነው በማለት መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ነው፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳት የደረሰበት የተጠሪ ተሽከርካሪ አመልካች በገባው የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረት ተጠግኖ ወደ ስራ እንዲመለስ በማለት ሊወስን ሲገባ ህጋዊነት በሌለው አግባብ የጉዳት ማስጠገኛ ግምት እንዲቀርብ በማድረግ የግምቱን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ መስጠቱ በብዙ መልኩ የአመልካችን መብት የጎዳነው በመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ብይን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ተሽሮ አመልካች ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ አስጠግኖ ለተጠሪ እንዲያስረክብ ተብሎ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎትም የአመልካች ተሽከርካሪ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ባደረሰው ጉዳት የተጠሪ ተሽከርካሪ መጠገን ይገባዋል እስከተባለ ድረስ አመልካች ተሽከርካሪውን እራሱ እንዲያስጠግን ሳይሆን ለጥገና ወጭ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት በሰበር እንዲታይ ተጠሪም በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡

ተጠሪም ሃምሌ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው የጽሁፍ ክርክር አመልካች በወቅቱ መኪናቸውን እንዲያስጠግን ተጠይቆ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በፍርድ እንደተወሰነና ቀደም ሲልም መኪናውን ለማስጠገን ሃላፊነት እንደሌለባቸው ጠቅሰው ሲከራከሩ የነበረ እንጂ እኔ ላስጠግን ይገባል በሚል በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት አለበት ከተባለ በቀጥታ ለዚህ ሰበር ችሎት ከሚቀርብ በቀር በይግባኝ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው የህግ ድጋፍ የለውም ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይንና ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አሰጣጥ አገልግሎት አይውልም!

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው የአመልካች ተሽክካሪ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ አመልካች ለጥገና የሚያስፈልገውን ወጪ ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት የሚመለከት ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ የሚያነሱት ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ወደነበረበት የመመለስ ዓለማ ከሆነ የጥገናው ዋጋ አሁን ካለው ተሽከርካሪው ዋጋ የሚበልጥ በመሆኑ ለተጠሪ መክፈል ያለአግባብ እንዲበለጽግ ያደርገዋል፣ ኢንሹራንሱ የመጠገን ሃላፊነት እያለበት የታለፈው ያለአግባብ ነው በሚል ነው፡፡

አመልካች ለጉዳቱ ሙሉ ለሙሉ ሃላፊ ነዉ የተባለ በመሆኑ አከራካሪ የሚሆነው አመልካች ለተጠሪ በግጭቱ ምክንያት ለደረሰባቸዉ ጉዳት የሚከፈለዉ ተመጣጣኝ ካሳ ምን ያህል ነዉ የሚለዉ ነዉ፡፡ ተመጣጣኝ ካሳ በመወሰን ረገድ ተሽከርካሪዉ ላይ የደረሰዉ ጉዳት ሙሉ ዉድመት ነዉ ወይስ አይደለም ተሽከርካሪው ተጠግኖ ከጉዳቱ በፊት ወደ ነበርበት ለመመለስ የሚያስፈልገዉ ወጪና ከጉዳቱ በፊት የነበሩ ወቅታዊ ዋጋ አንጻር ማነጻጸር የሚጠይቅ ሲሆን የተጠሪ ሃላፊነት መጠን የሚወሰነዉ ድርጊቱ ባስከተለዉ ጉዳት ልክ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ 2090 እና 2091 ድንጋጌ ይዘትም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንጻርም በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳት የደረሰበት መኪና ሊጠገን የሚችል ነው ወይስ አይደለም? ሊጠገን የሚችል ከሆነስ ለጥገናው የሚያስፈልገው ወጭ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ነጥቦች አጣርቶ እንዲወስን ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በመለሰው መሰረት ፍርድ መኪናው ሊጠገን የሚችል ስለመሆኑ እንዲሁም ለጥገና የሚያስፈልገውን ወጪ የእጅ ዋጋን ጨምሮ ከተለያዩ አካላት በማስቀረብ የተሽከርካሪዉን ትክክለኛ የማስጠገኛ ወቅታዊ ዋጋ እንዲሁም የጉዳቱ መጠን ላይ መሰረት በማድረግ ለጥገና 1,500,00 የሚስፈልግ ስለመሆኑ አረጋግጣል ይኸው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አልተለወጠም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በመመዘን የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና ወይም የማስረዳት ደረጃን የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ጥሰት እስካልተፈጸመበት ድረስ እንዳለ የሚቀበለው በመሆኑ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተመዘነን የሰነድ ማስረጃ እንደገና የመመዘን ስልጣን በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/2013 አንቀፅ

10 ያልተሰጠው በመሆኑ እንዳላ የሚቀበለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ለደሰው ጉዳት ማስጠገኛ የእጅ ዋጋን ጨምር የደረሱበትን ድምዳሜ አስመለክቶ የቀረበው ማስረጃ በመመርመር መወሰኑ የሥነ ሥርአት ግድፈት ፈጽሟል ወይም በባለሙያ ተጣርቶ የቀረበን ሳይመረምር ውሳኔ ሰጥቷል ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ አመልካች ይህንን አስመለክቶ የሚያነሳቸው ተቃውሞዎች ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች መኪናዉን አስጠግኖ የማስረከብ እንጂ ግምቱን የመክፈል ግዴታ እንደሌለበት ያቀረበዉን ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካች ግን ይህንን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያልተደረገበት መሆኑን መዝገቡ ያስገነዝባል፡፡ በእርግጥ ለተጠሪ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው ከላይ እንደተመለከተው በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ወደነበረበት ለመመለስ የሚያስችለውን መጠን እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329/1 እንደተደገገዉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳዉንና ያልቀረበዉን ክርክርና አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ለመቀበልና ዉሳኔ ለመስጠት እንደማይችል የተደነገገ ቢሆንም ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2 መሰረት በስር ፍርድ ቤት እንደ ክርክር ተነስቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ ሳይወሰን የታለፈ ከሆነ እና የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ ሆኖ ከተነሳ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ ዉሳኔ ሊሰጥበት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሳውንና ያልቀረበ ቢሆን አመልካችም በሰበር አቤቱታቸው ላይ የሚያነሱት በዋናነት በጠቅላላ የኢንሹራንስ ሕግ መሰረት ጉዳት የደረሰበትትን ተሸከርካሪ የመጠገን እና የመኪናው ቅሪት መረከብን የሚመለከቱ በመሆኑ የመድን ሰጪ ድርጅቶችን አሰራር ይጻረራል በማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን የሚመለከት በመሆኑ በአመልካች ተነስቶ በይግባኝ ወይም በሰበር ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ሌላው ያነሱት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ የተለየ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረብኩትን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው በማለት ያቀረቡት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 9(4) በግል የተመለከተውን መሰረት በማድረጉ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር ስህተት የተፈጸመበት ለማለት አልተቻለም፡፡

በአጠቃላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 400855 በየካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 88260 ሰኔ 09 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በማሻሻል የሰጠው እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 244965 በሚያዚያ 05 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ጸንቷል ፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**ትእዛዝ**</u>

በዚህ መዝገብ መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው አፈጻጸም እንዲታገድ ተሰጠው የአግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

<u>**መዝገቡ ተዘግቷል**</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!